# የገንዘብ ሚኒስቴር

# MINISTRY OF FINANCE

## መመሪያ ቁጥር 1023/2017
## ወደ አገር በሚገቡ እቃዎች ላይ ከተጣለው የማህበራዊ ልማት ቀረጥ ነጻ የሚሆኑ እቃዎችን ለመወሰን የወጣ መመሪያ

## DIRECTIVE Number 1023/2024
## A Directive to Exempt Goods from Social Welfare Levy Imposed on Import of Goods

መስከረም 2017 ዓ.ም
**September 2024**

# መመሪያ ቁጥር 1023/2017
# ወደ አገር በሚገቡ እቃዎች ላይ ከተጣለ የማህበራዊ ልማት ቀረጥ ነፃ የተደረጉ እቃዎችን ለመወሰን የወጣ መመሪያ

ለህብረተሰቡ በነጻ የሚሰጡ የትምህርት እና የጤና አገልግሎቶችን ለማስፋፋት እንዲሁም በሰው ሰራሽ እና በተፈጥሮ አደጋ ምክንያት ችግር ላይ የሚገኙ ወገኖችን ለመርዳት ከውጭ አገር በእርዳታ የሚላኩ እቃዎች የማህበራዊ ልማት ቀረጥ የተጣለበትን አላማ ለማሳካት የሚያግዙ በመሆኑ ከቀረጥ ነጻ እንዲሆኑ ማድረግ ተገቢ መሆኑ ስለታመነበት፤

ኢትዮጵያ በፈረመቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የተደረጉ እቃዎች ከዚህ የቀረጥ ዓይነትም ነጻ እንዲሆኑ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የገንዘብ ሚኒስቴር ወደ ሀገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ የማህበራዊ ልማት ቀረጥ ለማስከፈል የወጣ ደንብ ቁጥር 519/2014 አንቀጽ 6(3) መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "ከማህበራዊ ልማት ቀረጥ ነፃ የተደረጉ እቃዎችን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 1023/2017" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ

በዚህ መመሪያ ውስጥ:-

1/ **"ቀረጥ"** ማለት ወደ አገር በሚገቡ እቃዎች ላይ የማህበራዊ ልማት ቀረጥ ለማስከፈል በወጣው ደንብ ቁጥር 519/2014 የተጣለው የማህበራዊ ልማት ቀረጥ ነው፡፡

2/ **"ደንብ"** ማለት ወደአገር በሚገቡ እቃዎች ላይ የማህበራዊ ልማት ቀረጥ ለማስከፈል የወጣው ደንብ ቁጥር 519/2014 ነው፡፡

# DIRECTIVE Number 1023/2024
# A Directive to Exempt Goods to be Imported from Social Welfare Levy

WHEREAS, goods freely given to the public for improvement of education and health services and donated from abroad to assist citizens impoverished by natural and man-made calamities fulfill the intended purpose of the social welfare duty, it is deemed necessary to exempt them from the duty ;

WHEREAS, it has become necessary to exempt goods that has been exempted from taxes and duties under international agreements to which Ethiopia is a party from such kind of duty too;

NOW, THEREFORE, Ministry of Finance issued this directive in accordance with Article 6(3) of Social Welfare Levy on Imported Goods Regulation No.519/2022.

## 1. Short Title

This Directive may be cited as the "Directive to Exempt Goods to be Imported from Social welfare duty Number 1023/2024"

## 2. Definitions

In this Directive:

1/ **"Duty"** means the social welfare duty imposed on imported goods by Social Welfare Levy on Imported Goods Regulation No 519/2022;

2/ **"Regulation"** mean the Social Welfare Levy on Imported Goods Regulation No 519/2022.

## 3. ከማህበራዊ ልማት ቀረጥ ነጻ የተደረጉ እቃዎች

የሚከተሉት እቃዎች ከማህበራዊ ልማት ቀረጥ ነፃ ሆነው ወደ ሀገር ይገባሉ፡፡

1/ ለሚከተሉት የማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ከውጭ አገር በእርዳታ የሚላኩ እቃዎች ፡-

ሀ/ በመንግስት ባለቤትነት ስር ያሉ ወይም ለህብረሰሰቡ ነጻ አገልግሎት የሚሰጡ ፡

i) የትምህርት ተቋማት፤
ii) የጤና ተቋማት፤
iii) የሕጻናት፤ የሴቶች፤ የአረጋውያን፤ የአእምሮ ህመምተኞች እና የአካል ጉዳተኞች መርጃ ድርጅቶች፤

ለ/ በሰው ሰራሽ እና በተፈጥሮ አደጋ ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖች የአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ ለሚሰጡ ድርጅቶች ከውጭ አገር በእርዳታ የሚላኩ እቃዎች፤

2/ ኢትዮጵያ በፈረመቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ ሆነው ወደአገር እንዲገቡ የተፈቀደ እቃዎች፡፡

3/ የአገር መከላከያ ሚኒስቴር፣ የፌዴራል እና የክልል ፖሊስ ተቋሞች፣ የብሔራዊ መረጃ እና ደሕንነት አገልግሎት እና ኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር በሕግ በተፈቀደው መሰረት ወደ አገር የሚያስገቧቸዉ የመከላከያ እና የህዝብ ደህንነት መሳሪያዎች፣ ለነዚሁ አገልግሎት የሚዉሉ ክፍሎችና እና አክሰሰሪዎች፡፡

4/ በብሔራዊ ባንክ ወደ ሀገር የሚገቡ ሳንቲሞች፣ የገንዘብ ኖቶች እንዲሁም የብርና የወርቅ ጠገራዎች፡፡

## 3. Goods Exempted from Social Development Levy

1/ Goods donated from abroad to the following social welfare institutions shall be imported free from the Levy imposed by the Regulations;

a/ State-owned institutions or institutions rendering free service to the public listed here below;

(i) Education institutions;
(ii) health institutions;
(iii) organizations that help children, women, the elderly; mentally disabled and physically disabled.

b/ goods donated from abroad to organizations who provide emergency aid to persons affected by man-made and natural calamities.

2/ Goods that are exempt from taxes and duties under an international agreement to which Ethiopia is a party shall be imported free from Social development levy.

3/ Only defense and public security equipment, parts and accessories thereof imported by Ministry of National Defense, Federal police and Regional police institutions, Ethiopian National Intelligence and Security Services and the Information Network Security Administration in accordance to the law.

4/ Coins, bank notes, unwrought silver and gold imported by National Bank of Ethiopia.

## 4. ከቀረጥ ነፃ የማይሆኑ እቃዎች

## 4. Goods Not Exempted

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 3(1) የተመለከተው ቢኖርም ከዚህ በታች የተዘረዘሩት እቃዎች ከማህበራዊ ቀረጥ ነጻ ሆነው ሊገቡ አይችሉም፡-

ሀ/ ከስምንት መቀመጫ በታች ያላቸው አውቶሞቢሎች እና የእነዚህ መለዋወጫዎች፤

ለ/ ባለአንድ ወይም ባለሁለት ጋቢና ፒካፕ ተሽከርካሪዎች እና የእነዚህ መለዋወጫዎች፤

ሐ/ ለቢሮ አገልግሎት የሚውሉ ዕቃዎችና መሣሪያዎች፤

## 5. ማስረጃ ስለማቅረብ

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 3(1) ለተዘረዘሩት ተግባራት የሚውሉ እቃዎች ከቀረጥ ነጻ ሆነው ሊገቡ የሚችሉት የሚከተሉት ማስረጃዎች ሲቀርቡ ይሆናል፤

ሀ/ እቃዎቹ በእርዳታ የተገኙ መሆኑን የሚያረጋግጥ የእርዳታ የምስክር ወረቀት፤

ለ/ የእቃዎቹን ዝርዝር እና ዋጋ የሚያሳይ ኢንቮይስ፤

ሐ/ እቃዎቹ ለተገለጸው አላማ የሚውሉ መሆኑን እንዲሁም ስለእቃዎቹ አጠቃቀም ለገንዘብ ሚኒስቴር እና ለጉምሩክ ኮሚሽን ሪፖርት የሚቀርብ መሆኑ የሚያረጋግጥ አግባብ ባለው የመንግስት መስሪያ ቤት የተጻፈ የድጋፍ ደብዳቤ፤

## 6. የጉምሩክ ኮሚሽን ኃላፊነት

የጉምሩክ ኮሚሽን፡-

1/ በዚህ መመሪያ መሰረት ከቀረጥ ነጻ ሆነው ወደአገር የገቡ እቃዎች ሊከፈልባቸው ይገባ የነበረውን ቀረጥ መዝግቦ ይይዛል፤ ይህንኑ የሚያሳይ መረጃ በየሶስት ወሩ ለገንዘብ ሚኒስቴር ይልካል፤

2/ በዚህ መመሪያ መሰረት ከቀረጥ ነጻ ሆነው ወደ አገር የገቡት እቃዎች ወደ አገር

Notwithstanding the provisions of Article 3(1) of this Directive, the following goods shall not be exempted from social development levy:

a/ automobiles with less than eight passenger seats and their spare parts;

b/ pickup vehicles with one or two cabins and their spare parts;

c/ equipment and materials for office use.

## 5. Submission of Evidences

Goods destined for purposes listed under Article 3(1) shall only be exempt upon submission of the following evidences:

a) donation certificate showing that the goods are donated;

b) the list of items and an invoice showing their value;

c) a support letter from the appropriate government institution confirming that the goods will be used for designated purposes and assuring that a report will be submitted to the Ministry of Finance and the Customs Commission on the utilization of such goods.

## 6. Responsibilities of the Customs Commission

The Customs Commission shall**:**

1/ maintain records on the amount of Levy that shall have been paid on goods exempt from the Levy and submit quarterly reports to the Ministry of Finance on the same;

2/ carry out monitoring activities to ensure that goods imported free of the Levy in accordance with this Directive are used for the designated purposes and receive reports from government

ለገቡበት አላማ የዋሉ መሆኑን ለማረጋገጥ ክትትል ያደርጋል፤ ሪፖርት ይቀበላል፡፡

agencies who issued support letters;

## 7. የሚጸናበት ቀን

ይህ መመሪያ በፍትሕ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በገንዘብ ሚኒስቴር ይፋዊ ድህረ ገጽ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ**
**መስከረም 2017 ዓ.ም**

**አህመድ ሺዴ**
**የገንዘብ ሚኒስትር**

## 7. Effective Date

This Directive shall enter into force up on the date of its registration with the ministry of justice and uploading on the official website of the Ministry of Finance.

**Done at Addis Ababa**
**September 2024**

**Ahmed Shide**
**Minister of Finance**